**በጉምሩክ ኮሚሽን**
**የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**
**CUSTOMS COMMISSION**
**ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE**
**የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወሻ**

ቀን: 10/02/2012 ዓ.ም

ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ጣቢያዎች)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
ለ፡- ትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር የስራ ሂደት
ለ፡- ንግድ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፡- ወጪና ንግድ ያልሆኑ የገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፡- ገቢ ሂሣቦች አስተዳደርና የቀረጥ ተመላሽ የስራ ሂደት
ለ፡- ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የስራ ሂደት
ለ፡- ኢንተለጀንስ ኮንትሮባንድ ክትትል የስራ ሂደት
ለ፡ -ጉምሩክ ጉዳዮች ኤቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
ለ፡- ኢንዶዴ የጉ/ሥ/አ/ የስራ ሂደት
ለ፡- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት

ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
ኢ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ፍቃዱ አማረ /ተወካይ/

ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተሰጠውን የቀረጥና ታክስ ነጻ መብት ይመለከታል፤

በቁጥር 0.6/0100/12 በቀን 10/02/2012 ዓ.ም ከጉምሩክ ኮሚሽን እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/19 በቀን 6/2/12 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የአሉቶ ጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ማስፋፍያ ፕሮጀክትን ለማስፈጸም የሚያገለግሉ የመቆፈሪያ ማሽን መለዋወጫ ዕቃዎችና ለኃይል ማመንጫ ግንባታ የሚውሉ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲገባ የተሠጠው መብት ለሌሎች ፕሮጀክቶችም የሚያገለግል መሆኑን አሳውቆናል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ለሚያከናውናቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከቀረጥ ታክስ ነጻ እንዲያስገባ የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር አመ3/16/28/528/ በቀን 8/12/1999ዓ.ም እና በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/446 በቀን 26/4/2004 ዓ.ም የተላለፈ ውሳኔዎች በሌላ መመሪያ ያልተተኩ እና ጽኑ መሆናቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር የገለጸ ስለሆነ በዚሁ መሠረት አገልግሎቱ እንዲሰጥ እያሳሰብኩ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ 3 ገጽ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# CUSTOMS COMMISSION

ቀን ጥቅምት 10 2012
Date
ቁጥር 6-ዐ/0100/12
Ref.No.

**የጉምሩክ ስነስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**

**ባሉበት**

ጉዳዩ:- **የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተሰጠውን የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ይመለከታል፡፡**

ከአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር 01/መ10/05 በቀን 19/11/2011 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ አሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የአሉቶ ጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ማስፋፊያ ፕሮጀክትን ለማስፈጸም የሚያገለግሉ የመቆፈሪያ ማሽን፣ መለዋወጫ ዕቃዎችና ለኃይል ማመንጫው ግንባታ የሚውሉ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲገባ የተሰጠው መብት ለሌሎች ፕሮጀክቶችም የሚያገለግል መሆንና አለመሆኑን እንዲሁም ይህ መመሪያ በሌላ መመሪያ የተተካ መሆን እና አለመሆኑ ተገልጾ ማብራሪያ እንዲሰጥ በተጠየቀው መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/19 በቀን 6/2/2012 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ አሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ለሚያከናውናቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገባ በገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር አመ3/16/28/528 በቀን 8/12/1999 ዓ.ም. እና በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/446 በቀን 26/4/2004 ዓ.ም. የተላለፉ ውሳኔዎች በሌላ መመሪያ ያልተተኩ እና የፀኑ መሆናቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር የገለፀ ስለሆነ በዚሁ አግባብ አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብን፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፃፈውን ደብዳቤ 2 ገጽ ኮፒ አባሪ አያይዘን ልከናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዮናስ ተ[illegible]ልድ በላይነህ
የጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
ጽ/ቤት ኃላፊ

ግልባጭ/
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
  **ጉምሩክ ኮሚሽን**




☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No ቁ/ገ/ተ/14/19
ቀን
Date 6/2/2012

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የአሉቶ ጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ማስፋፊያ ፕሮጀክትን ለማስፈጸም የሚያገለግሉ የመቆፈሪያ ማሽን፣ መለዋወጫ ዕቃዎችና ለኃይል ማመንጫው ግንባታ የሚውሉ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ እንዲያስገባ የሚፈቅድ መመሪያ ሚኒስቴር መ/ቤታችን ማስተላለፉን፣ ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ ይህንኑ መመሪያ በመጥቀስ ለሌሎች ፕሮጀክቶችም የቀረጥና ታክስ ነጻ መብት እንደሚጠይቅና በጥያቄው መሰረትም ሲስተናገድ መቆየቱን ገልጻችሁ በመመሪያው ለኮርፖሬሽኑ የተሰጠው የቀረጥ ነጻ መብት ለሌሎች ፕጀክቶችም የሚያገለግል መሆንና አለመሆኑን እንዲሁም ይህ መመሪያ በሌላ መመሪያ የተተካ መሆን እና አለመሆኑ ተገልጾ ማብራሪያ እንዲሰጣችሁ 19/11/2011 በቁጥር 01/መ10./05 በተጻፈ ደብዳቤ የጠየቃችሁትን ይመለከታል፡፡

በዚሁ መሰረት፡-

1. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በአገሪቱ ላይ ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ለመሟላት ለሚያከናውናቸው የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ እና የዩኒቨርሳል ኤሌክትሪሲቲ አክሰስ ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም የሚያስመጣቸው ዕቃዎችና መሳሪያዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ እና በአገር ውስጥ በሚፈጽሟቸው ግገርዎች ላይ የሚከፍለው የተ.እ.ታ ደግሞ በተመላሽ ስርአት እንዲስተናገዱ ሚኒስቴር መ/ቤታችን 8/12/99 በቁጥር አመ3/16/28/528 ባስተላፈው መመሪያ ፈቅዷል፡፡

2. በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ለአሉቶ ጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎችን ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ እንዳስገባ ይፈቀድልኝ በማለት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት መ/ቤታችን ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የኢንቨስትመንት ስራዎች እንዲውሉ ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ ከላይ በተጠቀሰው መመሪያ መፈቀዱን፣ይህም መመሪያ በሌላ መመሪያ እስካልተተካ ድረስ የጸና መሆኑን ገልጾ የተጠቀሱት ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቅድ መመሪያ 26/4/2004 በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/446 አስተላልፏል፡፡

3. ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት መመሪያዎች ለኮርፖሬሽኑ የተሰጠው የቀረጥና ታክስ ነጻ መብት ለአንድ ለተወሰነ ፕሮጀክት ሳይሆን ኮርፖሬሽኑ በአገሪቱ ላይ የኤሌክትሪክ

Letter/sa

ስልክ
Tel 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No ቁ/ገ/ተ/14/19
ቀን
Date 6/2/2012

አቅርቦትን ለማስፋፋት ለሚያከናውናቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ መሆኑን እና እነዚህ መመሪያዎችም በሌላ መመሪያ እስካልተተኩ ድረስ የጸኑ መሆናቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህ መ/ቤታችን 8/12/99 በቁጥር አመ3/16/28/528 እና 26/4/2004 በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/446 በተጻፈ ደብዳቤ ባስተላለፋቸው መመሪያዎች መሰረት ለኮርፖሬሽኑ የተሰጠው የቀረጥና ታክስ ነጻ መብት በአጠቃላይ በኮርፖሬሽኑ ለሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መሆኑን እና መመሪያዎቹም በሌላ መመሪያ ያልተተኩ በመሆኑ የጸኑ መሆናቸውን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ቦቺ ስንታየሁ
የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

Letter/sa

ስልክ
Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98
251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia